**መግለጫ/ሜሞ'ራንዶም/**

ፌብሩዋሪ 8, 2024

*አመታዊ - መረጃ*

**Office of the School System medical Officer**
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Rockville, Maryland
ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
ሮክቪል፣ ሜሪላንድ

**ለ፡** ርዕሰ መምህራን በሙሉ

**ከ፡** Patricia Kapunan, MD MPH

**ጉዳዩ፡-** የበጀት አመት 2023–2024 ስለ Pediculosis (HEAD LICE)—የተሻሻለ ፖሊሲ

---

**አጭር መግለጫ**

የራስ ተባይ ቅማልን በተመለከተ የት/ቤቶች የጤና አጠባበቅ አፊሰር ያጋሩት ወቅታዊ መመሪያ።

**ዳራ**

ኦገስት 2023 በሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት የፀደቀው ወቅታዊ የጭንቅላት ተባይ ቅማልን የሚመለከት መመሪያ *የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከል፣ የአሜሪካ የሕፃናት ሕክምና አካዳሚ የቅርብ ጊዜ ተሞክሮዎችን ምክረሃሳብ ያንፀባርቃል።* (በትምህርት ቤቶች ውስጥ መደረግ ያለባቸው የቁጥጥር እርምጃዎች) እና የትምህርት ቤት ነርሶች ብሔራዊ ማህበር። ዋናዎቹ ለውጦች ከትምህርት ቤት ማግለል እና "ምንም-ቅጫም መገኘት እንደሌለበት" ከሚደነገገው ፖሊሲ ጋር ይዛመዳሉ። በቅማል ተባይ የተጠቁ ተማሪዎች እስከ ትምህርት ቀን መጨረሻ ድረስ በት/ቤት ሊቆዩ እና የመጀመሪያ ህክምናቸውን ካደረጉ በኋላ ወደ ትምህርት ቤት መመለስ ይችላሉ። እነዚህ *ለውጦች* የተደረጉበት ምክንያት ከዚህ በታች ተዘርዝሯል።

- ከጭንቅላት በላይ ¼ ኢንች የሆነ ቅጫም በቀላሉ የሚታይ አይደለም፤ እና የሚሳቡ ቅማሎችን የመፈልፈል ዕድሉ ዝቅተኛ ነው፣ ወይም እንዲሁ ባዶ ዛጎሎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ እነዚህ ቅጫሞች “የተባይ ሽፋን” ተብሎ ይታወቃል።
- ቅጫሞች በፀጉር ዘላ ላይ የሚጣበቁ ስለሆነ ወደ ሌሎች ሰዎች የመተላለፍ እድላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው።
- ከራስ ቅማል ተባይ ጋር ተያይዞ ባለው የተማሪዎች፣ የቤተሰቦች እና የማህበረሰቡ ስጋት ምክንያት አላስፈላጊ የሆነ ከትምህርት ቤት የመቅረት ሁኔታዎች በተባዩ ምክንያት ከሚከሰቱት አደጋዎች እጅግ የላቀ ነው።
- ቅማል በሚታይበት እና ማሳከክ በሚጀምርበት ጊዜ ግለሰቡ(ቧ) 4 እስከ 6 ሳምንት በቅማል ተይዞ(ዛ) እንደቆየ(ች) ያመለክታል። የቅማል ወረራ እና የመተላለፍ አደጋ የሚኖርበት ጊዜ በተለምዶ ከሚታሰበው ያነሰ በመሆኑ፣ ተማሪ እስከ ትምህርት ቀኑ መጨረሻ ድረስ እንዲቆይ/እንድትቆይ መፍቀድ በሐፍረት መገለልን ይቀንሳል፣ግላዊ ገመናን ይጠብቃል፣ እና በቤተሰብ ላይ የሚሆነውን አላስፈላጊ ሸክም ይቀንሳል።

ቤተሰቦች በፈቃደኝነት ተማሪዎቻቸውን ለህክምና ቀድመው መውሰድ ይችላሉ። የትምህርት ቤት ቡድኖች በከባድ የቅማል ወረራ ምክንያት በትምህርታቸው ላይ ጣልቃ በመግባት የማስቸገር ምልክቶች ላጋጠማቸው ተማሪዎች አስቸኳይ ግምገማ በማድረግ ህክምና እንዲወስዱ የመምከር አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ። ሥር የሰደደ ወይም ተደጋጋሚ የቅማል/ተባይ ወረርሽኝ ያለባቸው ተማሪዎች በሐኪም ወይም በጤና ባለሙያ የታዘዘ ሕክምና፣ወይም ሌሎች ድጋፎችን በሕክምና እና በመከላከል እንዲከታተሉ ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላሉ።

**መወሰድ ያለበት አስፈላጊ እርምጃ**

- ወቅታዊ የተሻሻለ *ህክምና እና እንክብካቤ (የራስ ቅማል/ተባይ) ሂደቶችን ይመልከቱ*
- *የበጀት ዓመት 2023-2024 (የራስ ቅማል/ተባይ) ህክምና እና እንክብካቤ የተሻሻለ መመሪያ* Google ፋይል፤ እንዲሁም የጽሑፍ ናሙናዎችን እና ትምህርታዊ ጽሑፎችን ያካትታል።

ከልዩ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ማንኛቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት ወይም ይህንን ፖሊሲ በተመለከተ ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ እባክዎን የትምህርት ቤቱን የሕክምና አፊሰር በዚህ ኢሜል SSMO@MCPSMD.ORG ያግኙ።

ያጸደቀው፡-

Betty J. Collins

2/5/2024

Dr. Betty J. Collins, Acting Deputy Superintendent — ቀን/Date